# የ ትውልድ

# That Generation

The Generation

ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 5 ቁጥር 5 ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

# ለትውልድ የተበረከተ ፮ኛ ዓመት

*(«ያ ትውልድ ተቋም» ምሥረታ ስድስተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

የ«ያ ትውልድ ተቋም»፡ ባለ ብዙ ቀለም ከሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ታሪክ በተለይ የየካቲት 1966ቱ አብዮት ከፈጠራቸው ብዙ ምክንያታዊ ሁነቶች ነው ትውልዱ። የየካቲቱ አብዮት የኢትዮጵያን ህዝብ፣ ኢትዮጵያ ምድሯን ትልቅ አውሎ ንፋስ እንደመታው ያልታደለ ከተማ፤ አፈር ድሜ አስግጦ ያደባየ፣ ምስቅልቅሉን ያወጣ በሀገራችን ህዝብ ታሪክ ውስጥ በለውጥ ጎደለኛነቱ፣ በታሪክ ድምቀቱ ወደር የማይገኝለት ትልቁ ታሪካችን ነው።

የየካቲቱ አብዮት ትልቅነቱ የታሪክ ደማቅነቱ ብቻ ሳይሆን የቀሰቀሰው ሹምሽር ህብረተሰቡን እንደ ካርታ ሲበውዘው፣ የሀገሪቱንም የቆዳ ስፋት አሳንሶታል። ይህ ግዙፍ ነውጥ የፈጠረውም ሹምሽር ግማሾቻችንን አፈር ድሜ ሲያስግጥ ገሚሶቻችንን ደሞ በለሆሰስ ነካ አርጎን አልፎአል። በመሆኑም! ይህ የታሪክ ሹምሽር በአዎንታም ይሁን በአሉታው በአዕምሮአችን ኖሮ በህሊናችን ያለፍነውን ታሪክ በምናይበት የህሊና ሰሌዳ ላይ እንደ ትራፊክ መብራት ብልጭ ድርግም ማለቱ አይቀሬ ነው። የትም ብንሆን።

እንግዲህ! «ያ ትውልድ ተቋም» የዚያ ዘመን ሁነቶች ከቀሰቀሱት የህዝብ ትግል ተወኔት ቅደም ተከተል አካል ሲሆን የትውልድ ዘሩን የሚቆጥረውም ከዚሁ ከ66ቱ የህዝብ ዓመጽ ነው።

ያ ትውልድ፤ የትውልድ ዘሩ ከዚያ ደፍራሳ ዘመን ይቆጠር እንጂ የአሁኑ ሰዓታት ውሎው ግን የጥንቱንም ይሁን የአሁኑን የፖለቲካ አካሄድ ለመድገም ሳይሆን ይልቁንስ የየካቲቱ አብዮት ታሪክ የተሸመነበት ድርና ማግ በመጎልጎሉ፤ ለማሳየት፣ ድምጽ ለማሰማት ነው። ምክንያቱም የጊዜያችን ታሪክ ውሉ የጠፋበት በመሰለበት በአሁኑ ጊዜ ታሪካችንን ለመጻፍ የተነሱት የታሪክ ከያንያን ታሪካችንን ከራሳቸው የፖለቲካ ምህዋር ውጪ በታሪክነቱ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በፖለቲካ ፍልስፍናቸው መለኪያ ውስጥ ታሪኩን ለመተረክ ስለሚሞክሩ ታሪካችን ብዥታ አጥቅቶታል። ለወትሮው እንኳ ታሪክ የሚጻፈው መጀመሪያው በአሸናፊው ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን በጊዜ ነው። አሁን የዛ ጊዜ አሸናፊዎች አልፈዋል።

የ«ያ ትውልድ ተቋም» እንዲመሰረት ምክንያት ከሆነው አንዱ የአንዳንድ ፀሐፊዎች የ66ቱን አብዮት ታሪክ ሲፅፉና በፖለቲካ ቡድኖች መሀል የነበረውን አሰላለፍ የሚያራምዱትን የፖለቲካ ፍልስፍና ሲተነትኑ በትንታኔያቸው የአብዮቱን የመሀል አገዳ ሁነቶች ከአውደ መረጃው ውጭ ስለሚያደርጉት የትንታኔያቸው መደምደሚያ የታሪክ ብዥታ፣ በታኝ በመሆኑ ነው።

ብኻ'ታውም የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄን፣ አልጀሪያ የገባውን የተማሪዎች ቡድን የአረብ "ቅጥረኛ"፤ በፍልስጤም ነጻ አውጭ ድርጅት የሰለጠኑትን ፋና ወጊ ጠንሻሽ ታጋዮችን "ሽብርተኛ"፤ በአሁኑ ጊዜ ማለቱ የደርግን የፕሮፖጋንዳ ማንፌስቶ ሙጥኝ ለማለት መሻት እንጂ ሌላ ቁም ነገር የለውም። የአንድን ፖለቲካ ድርጅት (በተለይ የኢሕአፓን) የፖለቲካ አመለካከት፡ በበቃ አእምሮ መፈተሽ፣ መመርመር፣ አሊያም መቃወም የተገባ ቢሆንም በአሉባልታ ወሬ ጥላቻን ይዞ ድርጅቱ ያልነበረውን ቀለም ቀብቶ የቅጽል ስም መስጠት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ጥበብን እሻለሁ የሚል ሁሉ ለዜና ቀያሪ ሁነቶች ፍቃዱን ማሳየት ይገባዋል። አለበለዚያ ግን የታሪክ ትንታኔው ሰበብ እና ውጤት ይጎድለዋል። ያንን የ66ቱን ዘመን መለስ ብለን አሁን ስንመለከተው የኢትዮጵያ አብዮት ካስቆጠረው ሞት፤ በአብዛኛው ሕይወታቸውን ያጡት የኢሕአፓ ልጆች ናቸው። እነኝህ ልጆች ሕይወታቸውን ያጡት ደርግና እድምተኞቹ እንደሚሉት "ፀረ-አብዮተኛ"፣ "ቅጥረኛ"፣ "ሽብርተኛ" በመሆናቸው ነውን? ይህ አስተሳስብ ያኔም ይሁን ዛሬ በታሪክ ሚዛን ላይ ሲወጣ ሚዛን አያነሳም።

"የታሪኩን ንግርት ለባለታሪኩ ተውለት" ይላሉ አበው። እና የነኛን ታላቅ ትውልድ ታሪክ፣ የኢሕአፓን ታሪክ መጻፍ ካስፈለገ ደግሞ ታሪኩን ከባለታሪኩ የተሻለ ተራኪ ላሳር ነው።

እንግዲህ የ «ያ ትውልውድ ተቋም»፡ አመጣጡ ከብዙ በጎ ምኞት እና ፍቃድ ታሪኩን በባለታሪኩ እንዲጻፍ ለማበረታታት እና ያ ክፉ ዘመን እንዳይደገም አስታዋሽ ለመሆን ነው። ስለሆነም፤ የዓላማ ብዙ ዘርፎች አሉት።

ዓላማዎቹም፦

- ከ1953 ዓ.ም. እስከ 1991ዎቹ፡ በኢትዮጵያ የታየው የለውጥ ሁነቶች በደምብ ባለመጻፋቸው እናም በተለይ የ1966ቱ እስከ 1970ዎቹ የነበረውን ለውጣዊ ክስተት እውነቱ በሁለት እግሩ ቆሞ እንዲታይ ለመርዳት የመረጃ ምንጭ ለመሆን።
- ለተሰውት ጓዶች መታሰቢያ ሀውልት ለማቆም።
- የበጎ አድራጎት ሥራ ለመስራት ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም»፡ እነኝህን ዓላማዎች ይዞ ሲነሳ ከላይ ያጣቀስናቸው ቁም ነገሮች እንዲህ በቀላሉ የሚተገበተሩ እንዳልሆኑ ግልጽ እንደሚሆን እምነታችን ነው። ስለሆነም! የ«ያ ትውልድ ተቋም» የስድስት ዓመት ልደቱን በሚያከብርበት ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም. (July 05, 2018) ወቅት ይህ ጉዳይ ይመለከተኛል ለሚል የዚያ ታላቅ ትውልድ ወገን ሁሉ ይህንን እረጅም ታሪካዊ ጉዞ አብረን እንድንጓዝ መልዕክታችንን ስናስተላልፍ፣ ስንጠይቅ በታላቅ አክብሮት ነው።

"ታሪካችሁ ህያው ነው" ብለን የዛሬ ስድስት ዓመት በሰሜን አሜሪካ ዳላስ ከተማ ከሰኔ 28 -29 (July 05 - 06, 2018) 2004 ዓ.ም. በአደረገው መሥራች ጉባዔ የተመሠረተው "ያ ትውልድ ተቋም" ለመላው የያ ትውልድ ቤተሰብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን አደረሳችሁ እንላለን።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለሕዝብ መንግሥት ምሥረታ በተካሄደው ሕዝባዊ ትግል በርካታዎች ሕይወታቸውን ከፍለውበታል። አካላቸውን አጥተዋል። ይህ የተከፈለ መስዋዕትነትና የያ ትውልድ የትግል ታሪክ ለትውልድ በመረጃነት በመጠበቅ፣ በማስቀመጥና በማስተላለፍ ትምህርት ይወሰድበት ዘንድ «ያ ትውልድ ተቋም» ይዞ የተነሳው ዓላማ በዚህ ስድስት ዓመት ጉዞ የተቻለውን ውጤት አስመዝግቧል እንላለን።

ለተነሳበት ክቡር ዓላማ ለሕዝብና ለሀገር አንድነት፣ ለሰው ልጆች መብት፣ ለተበዳዩ ሕዝብ ግንባር ቀደም ፋና ወጊ ሆኖ ከፋሽስት ደርግ መንግሥት ጋር ሲፋለሙ እስከወዲያኛው ያሸለቡ ብርቅዬ

የኢትዮጵያ ልጆች ታሪካቸው መፃፍ፣ መነገር፣ መነበብ ይኖርበት ዘንድ የመረጃ ምንጭ ለመሆን የያ ትውልድን የትግል ውጣ ውረድ መረጃ በማሰባሰብ እየተንቀሳቀሰ ያለው «ያ ትውልድ ተቋም» የተመሰረተበትን ስድስተኛ ዓመቱን ሲያስታውስ አሁንም ሰማዕታት ወገኖቻችንን ከፍ እያደረግን ነው።

ያ ትውልድ ተቋም በጠንካራ አባላቱና ደጋፊዎቹ እገዛ ስድስት ዓመት የመጓዙ ምስጢሩ በሥራና በተግባር የሚታይ ክንዋኔ በማስመዝገቡ ነው። በአለን አቅም ታሪካዊ ወቅቶችን በማስታወስ፣ በማስነበባችን ነው። በመረጃ ክምችታችን "ያ ትውልድ" ድረ ገጽ ያካተትናቸው መረጃዎች ለተጠቃሚዎች የመረጃ ምንጭ በመሆናቸው ነው። አስተዋሽ ያጡ የያትውልድ ሰማዕታት በተለይ በደርግ አንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ሰለባዎች ስምና ምስል ማካተታችን በርካታ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ቤተሰቦችን በማስደሰቱ ነው።

አንዱ ጥረታችን አኩሪ ታሪካችንን መንከባከብና ለትውልድ ማስተላለፍ ነውና በዚህ ስድስት ዓመት ተመክሮአችን ጠንካራ ጎናችንን ይበልጥ እያጎለበትን ደከም ያልንበትንም እየመረመርን ስንጀምርም ራዕያችን፣ ተልዕኮአችን ብለን የተነሳንበትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴአችን የማያቋርጥ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ ተስፋ አለን።

ታሪክን በስማ በለውና እንዲህ ነበር ተብሎ በሦስተኛ ወገን ከሚነገር ይልቅ ባለታሪኩ እራሱ ኃላፊነቱን ወስዶ ቢያሰባስበው ይመረጣል። ድሮ "ታሪክ ሰሪው ሰፊው ሕዝብ ነው" ሲባል፤ የዐድዋ፣ ማይጨው ታሪክ የሕዝብና ሀገር ታሪክ ናቸው ለማለት ነው። ጥሩ መንግሥት ኖረ አልኖረ፡ ታሪኩ ሳይዛባ ይጻፍ፣ ይሰበሰብ ዘንድ ቅን አሳቢዎችና ሀገር ወዳዶች ይጥራሉ። የያ ትውልድም ታሪክ ከዚህ የሚለይበት ጉዳይ የለም። የታሪኩ "ብቸኛ" ባለቤት ነኝ ባይ ሊኖር አይገባም። የትውልዱ፣ የሀገርና የሕዝብ ታሪክ ነውና። በመሆኑም ስለ ያ ትውልድ መረጃው ያለውና ችሎታ ያለው ሊጽፍ፡ ሊተርክ፡ በፊልም ሊሠራው ይችላል። ችግሩ ግና መጻፉ ላይ ብቻ ሳይሆን መረጃዎቹን ማግኘት ላይ ነው። የመረጃዎችን እጥረት ለመቅረፍና በዘመናችን የኢንተርኔት መረጃ ሥልጣኔ ያለምንም ውጣ ውረድ በቀላሉና በነፃ ተጠቃሚዎች ማለትም ለተመራማሪዎች፡ ለጸሀፊዎች፡ ለመማሪያነት ለሌላም ተግባራት ለሚፈልጉ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ አካላት እና ሌሎች በቀላሉ ያገኙ ዘንድ «ያ ትውልድ ተቋም» የጀመረው ጉዞ በተጠናከረ መልኩ እንደሚቀጥል ስድስተኛ ዓመታችንን ስናስታውስ ለመግለጽ እንወዳለን።

ያ ትውልድ ብለን ስንነሳ በዋናነት በ1960ዎቹ የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ የተሳተፉትንና በተለይ በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው ከፋሽስቱ የደርግ አገዛዝ ጋር ሲፋለሙ በደርግ የትውልድ ማጥፋት ቤት ለቤት አሰሳ፣ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ጭፍጨፋ ሰለባ የሆኑትን ወገኖች በዋናነት ይመለከታል። ሆኖም ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ከባዕዳን ወራሪዎች ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን የከፈሉና አኩሪ ታሪክ አስመዝግበው ያለፉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያንን፣ በተለያዩ የጭቆና አገዛዝ መረቦች ውስጥ ተቀፍድዶ የተያዘውን ሕዝባችንን ለዜግነት መብቱ መከበርና ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታ ሲፋለሙ የአምባገነን አገዛዞች ሰለባ የሆኑትን ወገኖች ከያ ትውልድ ዘመን በፊትም ሆነ በኋላ ያሉትን ይመለከታል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ቀደም ሲል በ1969 ዓ.ም. የዓለም ሠራተኞች ቀን ክብረ-በዓልን አስመልክቶ በሰላማዊ ሰልፍ ለማክበር በወጡ ወጣቶችና ሕፃናት ላይ በደርግ አገዛዝ የደረሰውን ፍጅት መታሰቢያነት፤ በሜይ ዴይ ማለትም ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም የ«ያ ትውልድ ተቋም» ድረ ገጽ www.yatewlid.org or www.yatewlid.com ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ መደረጉ ይታወቃል። ይህ ድረ ገጽ በተለይ 1969/72 በደርግ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን ሰማዕታት ስምና ምስል ከማካተቱም በተጨማሪ በወቅቱ ይወጡ የነበሩ ድርጅታዊ ልሳኖችን (ለምሳሌ በኢሕአፓ በኩል "ዴሞክራሲያ"፣ በመኢሶን በኩል "የሰፊው ሕዝብ ድምጽ" ) እና ሌሎችንም መጣጥፎችን ያካተተ የመረጃ ክምችት (ዳታ ቤዝ) ነው።

በዚህ መልኩ የተንቀሳቀሰውና ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. መሥራች ጉባኤውን በዳላስ ከተማ ያደረገው «ያ ትውልድ ተቋም» በስድስት ዓመት ጥረታችን ድረ ገጹ የእንግሊዘኛ ክፍል እንዲኖረው በማድረግና ያልተካተቱ በርካታ ሠነዶችን በማካተት በአዲስ መልክ አዘጋጅተነዋል። በተጨማሪም www.redterror.org, www.thatgeneration.org ድረ ገጾች የድረ ገጹ መግቢያዎች ይሆኑ ዘንድ እንደሚያገለግሉ ስናሳውቅ በታላቅ ደስታ ነው።

***ያ ትውልድ ያስመዘገበውን አኩሪ የፍትህ ተጋድሎና የከፈለውንም መስዋዕትነት ለማስታወስና ተተኪው ትውልድ ካለፈው ትውልድ ታሪክ በመቅሰም ለሀገሩና ለሕዝቡ ተሟጋች ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ መሠረት የሚጥል፣ በያ ትውልድ ስም የሚንቀሳቀስ የትውልድ መታሰቢያ ተቋም ከተቋቋመ እነሆ ስድስት ዓመት ሞላው።***

«ያ ትውልድ ተቋም» በቀጣይነት በተለማቸው የአጭርና እረዥም ጊዜ ዕቅዶች መሠረት በመረጃ ማሰባሰብ ሂደቱ ያሉትን ክፍተቶች ማሟላት እንደሚጠበቅብን በመገንዘብ አሁንም ለያ ትውልድ ወገኖችና ቀና ሀሳቢዎች እያደረጋችሁ ያላችሁት ትብብር ይቀጥል ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።
«ያ ትውልድ ተቋም» ያለብንን የገንዘብ አቅም ለመቅረፍ በተለያየ ጊዜ ትብብር ላደረጋችሁልንና እያደረጋችሁልን ላላችሁ ወገኖቻችን በሰማዕታት ወገኖቻችን ስም ምስጋናችን ይድረሳችሁ እንላለን። በያ ትውልድ ድረ ገጽ ያልተካተቱ ሰማዕታትን ስምና ምስል በመላክ የምናደርገው ጥረት የራሳችሁ አድርጋችሁ የተባበራችሁንን ሁላ እያመሰገንን አሁንም «ያ ትውልድ ተቋም»ን በማጠናከር በትግሉ የወደቁ ወገኖቻችንን ከፍ ከፍ እናድርጋቸው እንላለን። እጅግ በጣም በርካታ የያ ትውልድ የትግል ታሪክ መረጃዎች የሀገርና የሕዝብ ሀብት ናቸውና ለተጠቃሚዎች ክፍት እናደርጋቸው ዘንድ እንተባበር እንላለን።

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነፃ ሆኖ በትግሉ ላለፈው ትውልድ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የትግሉን ታሪክ እውነተኛ መረጃ በማሰባሰብ፣ የተጎዱ ወገኖችን በመርዳትና ለትውልዱ የስም መጠሪያ ይሆን ዘንድ መታሰቢያዎችን በማቆም ላይ ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

***ራዕይ***

ፍትህና የሕግ የበላይነት በሰፈነባት ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ የትውልዳችንን ታሪክ በሚገባ በመጠበቅና ለታሪክ በማኖር ቀጣዩ ትውልድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪና ታሪክ ተረካቢ ብቁ ዜጋ ሆኖ ማየት።

**ተልዕኮ**

የታሪክ ቅብብሎሽ ይቀጥል ዘንድ ከሚሠሩ ወገኖች ጋር በመተባበር የያን ትውልድ የትግል ታሪክና የተከፈለውን መስዋዕትነት መረጃ ማሰባሰብ፣ ትውልዱ በታሪክ ሲታወስ ይኖር ዘንድ መታሰቢያ ማቆምና በትግሉ የተለያየ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች አቅም በፈቀደው መጠን መንከባከብ፣ መርዳት።

***ዓላማ***

የያ ትውልድ ተቋም ዓላማ ለሉዓላዊትና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ የተደረጉ የትግል ታሪኮችን መረጃ በማሰባሰብ፣ በዚህም ትግል ክቡር ሕይወታቸውን ለሰጡ ሰማዕታት መታሰቢያ ማቆምና በስማቸው ለወገናችን ልማት ተኮር ግብረ-ሠናይ ተግባራትን ለማከናወን ኢትዮጵያውያንን ማስተባበር ነው።

የትውልዳችንን ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ እንተባበር!

***«ያ ትውልድ ተቋም»*** ሰኔ 28 ቀን 2010 ዓ.ም. (July 5, 2018)

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, **ምሥለ ገጽ** (Facebook) ፡ yatewlid
website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
http://www.redterror.org , http://www.thatgeneration.org